**ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ወደ ዓለም መጣ?**

**ዓለምን ለማዳን መጥቶ የፈጸማቸው ተግባራት ዋና ዋናዎቹ እነሆ፤**

በ2001 ዓ.ም. የጌታችን ልደት በዓል በሚከበርበት ዕለት አገለግልባትና እገለገልባት በነበረች ቤተ-ክርስቲያን ምዕመኑ ሁሉ ተሰብስቦ በዓሉን እያከበርን ሳለን የቤተክርስቲያኒቱ የሽማግሌዎች ሰብሳቢ ፕሮግራሙን ይመራ ስለነበር መጨረሻ ላይ "ጌታ ኢየሱስ ለምን ወደ ዓለም መጣ?" የሚል ጥያቄ ደጋግሞ ጠየቀና እኔን በቃል እንዳገለግል ጋብዞኝ ከመድረክ ወርዶ ተቀመጠ። እኔም በዕለቱ ላቀርበው የተዘጋጀሁበት ትምህርት በዚሁ ርዕስ ነበርና በሁኔታው መገጣጠም ተገርሜ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ትምህርት አካፈልኩ። ይህ ትምህርት ሁሉም ክርስቲያን ሊያውቀው የተገባ ስለሆነ አሁን በኦንላይን ማካፈል አስፈላጊ ሆኖ ታየኝ።

ጌታ ኢየሱስ ወደ ዓለም የመጣበት ምክንያት ዝርዝር ብዙ ቢሆንም እነዚያን ሁሉ እያደር መጽሐፍ ቅዱስን ይበልጥ እያጠኑ ስኬድ የሚደረስባቸው ስለሆነ ለአሁኑ የተወሰኑ አብይ የሆኑ የመጣባቸው ጉዳዮች ከዚህ በታች ሰፍረዋል።

1. **መለያትንና ጠላትነትን ለማስወገድ፣ የጥልን ግድግዳ በማፍረስ ወደ አንድነት ለማምጣት፤**

- የሰው ዘርን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቅ፦ በኃጢአታችን ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ጥለኛ ሆነን/ርቀን የነበርነው አህዛብ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበንና ሊያስታርቀን፣ በእኛና በእርሱ መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ ሊያፈርስ መጣ። የእግዚአበሔር ማዳንና የበረከት እጅ እንዳይዘረጋልን ኃጢአታችን በእኛና በእርሱ መካከል ገብታ ለይታን እንደነበር ኢሳያስ 59፡1 ያስረዳል። ሮሜ 5፡9-10 የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን በልጁ ሞት ከእርሱ ጋር ከታረቅን፣… ይላል 2ቆሮ 5፡18-19፣

  ኤፌ 2፡16-18፣ "ጥልን በገደለበት በመስቀሉም ሁለቱን በዚህ በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ። [17] መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁት ለእናንተ፣ ቀርበው ለነበሩትም ለእነርሱ ሰላምን ሰበከ፤ [18] ሁላችንም በእርሱ አማካይነት በአንዱ መንፈስ ወደ አብ መቅረብ እንችላለንና።"

  1ጢሞ 2፡5፤ "አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤"

- በሰው ዘሮች መካከል ያመኑት ከየትኛውም ሀገር ነገድና ቋንቋ ቢሆኑ እርቅና ህብረትን (አንድነትን) የአንድ ቤተሰብ አባልነትን ሊመሰርት። ሮሜ 12፡4-5 "እኛ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን።" (1ቆሮ12፡27)

- በብሉይ ኪዳን ዘመን ሁለቱም ማለትም እስራኤላውያን ከአህዛብ ጋር ህብረት ያልነበራቸው ሲሆን አህዛብም (እስራኤላውያን ያልሆኑ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ) በአንድነት ለአብርሐም የተሰጠ የበረከት ተስፋ ቃል አብረው ወራሾች እንዲሆኑ ለማስቻል። የእግዚአብሔር ሃሳብ በአንድ አገር ያለ የተለያየ ብሄረሰብ ብቻ ሳይሆን የዓለም ህዝብ ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ የአንድ አባት ልጆች/ የአንድ ቤተሰብ አባላት፣ የእንዲት ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ዜጋ ማድረግ ስለነበር፤ ይህም ጌታ ኢየሱስ ወደ ዓለም በመምጣቱ አከናውኖታል። ሐሥ 17፡26-27፣ ኤፌ 2፡11-14፣16።

- እስራኤላዊያን እንኳ ሆነው ከህዝቡ በኃጢአትና እንደ ለምጽ ባሉ በሽታዎች ምክንያት የተገለሉትን ሰዎች ለምጻሞችን፣ በዕውርነትና በበሽታ ምክንያት በልመና የሚተዳደሩትን/ድሆች ሆነው የነበሩትን፣ በአጋንንት ታስረው እንደ ዱር እንስሳት ከሰው ተለይተው ቀንና ሌሊት ክረምትና በጋ ከቤት ውጪ በመንከራተት ይኖሩ የነበሩትን፤ ከማህበረሰቡ ይገለሉ የነበሩትን እየፈወሰና ነጻ እያወጣ ከማህበረሰቡ ጋር አቀራረባቸው (ተቀባይነት እንዲኖራቸው አደረገ)።

- ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ወደ አንድነትና ሕብረት የሚያመጣው ከማንኛውም አገር ቢሆኑ በእርሱ ያመኑትን ነው እንጂ የወንጌልን እውነት ከሚቃወሙት ጋር አይደለም። የወንጌሉ ቃል

ከማይቀበሉትና የሃሰት ትምህርት ለማስተማርና ለመከተል ከመረጡት ማለትም ወንጌልን ከሚቃወሙት ጋር ግን ሊለያይ ማለትም አስተምህሯቸውንና አኗኗራቸውን እንዳንቀበልና እንዳንከተል ለማድረግ የመጣ መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ሉቃ 12፡49-53፣ ዮሐ 7፡40-43፡፡

**ስንዴውን ከገለባው ሊለይ፤** (የእግዚአብሔር ወይም የዲያብሎስ ወገን የሆኑትን ማለትም በጌታ የሚያምኑትን የእግዚአብሔር ወገን መሆናቸውና የማያምኑት የዲያብሎስ መሆናቸውን ሊለይ) ማቴ 10፡ 34-37፣ 12፡30፣ 25፡31–46፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በጌታ ኢየሱስ ያመኑቱ ያላመኑትን ሰዎች ማራቅና ማግለል ሳይሆን የገባቸውን መንፈሳዊ ዕውነት በፍቅርና በትዕግስት፣ በአክብሮትና በትህትና ለመንገር፣ በተግባርም ክፋት ባደረጉባቸው ፊንታ ለእነርሱ መልካም ለማድረግ በመጣር ጌታን ያላወቁትና ያላመኑት በክርስቶስ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

**2.በእርሱ የሚያምኑትን የሰው ዘር ሁሉ/ዓለምን ለማዳን** …. ዮሐ 3፡16-17, 12፡17፣ ሉቃ 2፡8-12፡፡

ይሄ የማዳን ስራ ያከናወነው በሁለት ደረጃዎች/ምዕራፎች ነው፡፡

2.1. የእግዚአብሔርን መንግስት **የምስራቹን ወንጌል በማብሰር፣ በመስበክ፣ በማወጅ የጠፉትን በጎች በመፈለግ/ኃጢአተኞችን ወደ ንስሃ ለመጥራት፡፡ እንዲሁም የዳኑትም እንዴት በእግዚአብሐር ፊት መኖር እንዳለባቸው ለማስተማር፡፡** ማር 1፡14-15, 2፡2፡17፣ 35-38፣ ሉቃ 4፡42-44፣ 10፡8፣11፣ 1ጢሞ 1፡15፣

ጌታ ኢየሱስ ዕድሜው 30 ዓመት አካባቢ ሲደርስ በብሉይ ኪዳን የመሲሁ መምጫ ጊዜ በማያሻማ ሁኔታ የተገለጠ ስላልነበረ ለጠፉት በጎች/ለኃጢአተኞች፣ በጨለማ ለነበሩት፣ ትጠባበቁት የነበረው የመሲሁ መምጫ ጊዜ አሁን ነው፤ የእግዚአብሔር መንግስት በመካከላችሁ አሁን በኃይል መስራት ጀምሯል፣ መሲሁ /የእግዚአብሔር ልጅ/ እኔ ነኝ፣ በኔ እመኑ እያለ ይሰብክ ነበር፡፡ ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔር የወሰነው የመሲሁ መምጫ ጊዜ ደርሶ መሲሁ በመካከላቸው መሆኑን ሊገልጥ፣ ከአዳም ዘመን ጀምሮ ተበላሽቶ የነበረው የእግዚአብሔር መንግስት ከሰው ዘር ጋር የነበረው የቅርብ ግንኙነት/ሕብረት በምድር ወንጌልን በመስበክ እንደገና ሊያድስና ሊመሰርት፣ ሊያስፋፋም መጣ፡፡ ሉቃ 4፡18-19፣42-44፡፡

የአዲሱ መንግስት አመራር ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ከቀድሞ አካሄዳቸው ንስሀ በመግባት የሚነገራቸውን በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር መንግስት አሰራር እውነት ቃል በእምነት እንዲቀበሉ ለመስበክ፡፡

**2.2. ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ በመስጠት፤ እንደ መስዋዕት በግ በመታረድ፣ ደሙን በማፍሰስ፣ ለእኛ ስለ ኃጢአታችን የተገባን የእግዚአብሔር ቁጣና የሞት ፍርድ በእኛ ፊንታ በመቀበል፤ ከባላጋራዎቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ በማዳን** አምላካችን ለእምነት አባቶች (ለአዳም፣ ለአብረሃም፣ ለዳዊት ዘፍ 3፡15፣ 12፡3፣ 2ሳሙ 7፡12) የሰጠውን የተስፋ ቃል ሊፈጽምና ወራሾች ሊያደርገን መጣ፡፡ ሉቃ 4፡18-21፣ ሉቃ 1፡68-75፣ ማር 10፡45፣ ቲቶ 2፡13-14፣

ጠላቶቻችን እነ ማን/ምንድር ናቸው? ጌታ ኢየሱስ ተዋግቶ ያሸነፈልን ጠላቶቻችን ዝርዝር ከዚህ በታች ሰፍረዋል፡፡

**ሀ. ማቴ 1፡20-21፣ 20፡28፣ ይገዛን የነበረ ኃጢአት (ከኃጢአት ባርነት)፡-** ኃጢአታችን ሁሉ ከኛ ወስዶ እርሱ በመሸከም ለኛ የተገባውን አሰቃቂ ቅጣት ሁሉ እርሱ ተቀብሎ ለኛ የመስዋዕት በግ ሆኖ በደሙ የኃጢአት ይቅርታና ከእግዚአብሔር ጋር እርቅና ሰላም

ሊያስገኝልን/ቤዛ ሊሆነን፡፡ ዕብ 9፡25-28፣ 1ጴጥ 2፡24

**ለ. ገላ 3፡13**፣ በእንጨት ላይ የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ስለተጻፈ ክርስቶስ

ስለኛ እርግማን ሆኖ **ከህግ እርግማን ሊዋጀን** (ነጻ ሊያወጣን) መጣ፡፡

**እርግማን**፡- ትዳር፣ የወለዱት ዘር፣ ለመተዳደሪያነት የሚሰሩት ማንኛውም ዓይነት ስራ እንዳይባረክ፤ ከጭለማው ኃይላት/ከአጋንንት የሚመጡ ልዩ ልዩ ክፉ ተጽእኖ፣ጭንገፋና እስራት፣ ድርቅና ጦርነት፣ የጎርፍ ጥቃት... እየጨመረ እንጂ እየቀለለ የማይሄድ የተደራረበ ችግር በሰው ላይ አስከትሎ ነበር። በብሉይ ኪዳን ዘመን ሕግ የተሰጠው ለእስራኤላዊያን ብቻ የነበረ ቢሆንም አህዛብም የተሰጣቸውን የሕሊና ሕግ የተላለፉ በመሆኑ አዳም በኃጢአቱ እንደ ተረገመው ያው ከእግዚአብሔር ቁጣ በታች ነበሩ።

**ሐ. ከሁሉም ዓይነት በሽታና ሕመም ሊፈውሰን** (ኢሳ 53፡5፣ ማቴ 8፡16-17)

ጀርባው በጅራፍ በመገረፍ፣ እጆቹና እግሮቹ በምስማር በመቸንከር፣ ጎኑ በጦር በመወጋት፣ ራሱ ላይ የእሾህ አክሊል በመድፋት ሁለንተናው ቆስሎ፣ አሰቃቂ ስቃይና ሕመም የተቀበለው በጨለማው ኃይላት ከሚመጣ የጤና ቀውስ ብቻ ሳይሆን በሽታ አምጪ ከሆኑ ፍጥረታትና ነገሮች ከሚመጣ በሽታም ሁለንተናዊ ፈውስ እንዲሆንልን ነው።

1ኛ ጴጥሮስ 2፥24፣ “ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በእንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ፤ በእርሱ ቊስል እናንተ ተፈውሳችኋል።”

ጥቅሱ እንደሚናገረው በኃጢአታችን ንስሃ ገብተን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ከጀመርን በኋላ ቀድም ያደርጉት የነበረን ኃጢአት በመተው ጌታ ኢየሱስ ያስተማረውን ትምህርት በመከተል መልካም ፍሬ በማፍራት የሚቀጥል አማኝ በበሽታ ከመጠቃት ይጠበቃል፤ ቢታመምም ራሱ በእምነት ጸልዮ ወይም ሌሎች የወንጌሉ ቃል አገልጋዮች ጸልየውለት ይፈወሳል ማለት ነው። ደጋግሞ ኃጢአት በማድረግ የሚቀጥል አማኝ ግን ብዙ በበሽታ ሊጠቃ ይችላል።

**መ. ከሥራ ሕግ/ከኃጢአት ኃይል በታች (ተገዢነት) ከመሆን ነጻ አውጥቶ ከጸጋ ሕግ በታች ሊያደርገን መጣልን።**

ሮሜ 6፡14፣ “ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስላልሆናችሁ፣ ኀጢአት አይገዛችሁምና።”

ኤፌሶን 2፥15 “ሕግንም፣ ከትእዛዛቱና ከሥርዐቱ ጋር በሥጋው ሻረ። ዐላማውም ከሁለቱ አንድን አዲስ ሰው በራሱ ፈጥሮ ሰላምን ለማድረግ ነው።”

ቆላስይስ 2፥14፣ “ሲቃወመንና ሲጻረረን የነበረውን የዕዳ ጽሕፈት ከነሕግጋቱ በመደምሰስ፣ በመስቀል ላይ ቸንክሮ ከመንገድ አስወገደው።”

**ሠ. የዲያብሎስና የጨለማው ኃይላት ስራ በማፍረስ ከእነርሱ ተገዢነት ነጻ አውጥቶ መልሶ እነርሱን የመግዛት ሥልጣን ሊሰጠን መጣ፣** ቆላ 1፡13፣ 2፡15፣ ዕብ 2፡14-15፣ 1ዮሐ 3፡8፣ ሉቃ 10፡19።

እግዚአብሔር የምድር ፍጥረታትንና ሰውን ከፈጠረ በኋላ ሰውን የምድር ፍጥረታት ሁሉ ገዥ አድርጎ ሾሞት ነበር። የሰው የቅርብ ኃለፊና የበላይ ባለስልጣን እግዚአብሔር ብቻ ስለነበር በሰው ላይ ሌላ የበላይ አልነበረም። ሰውም ምድርንና የምድር ፍጥረታትን ሁሉ የመግዛት ስልጣን ተሰጥቶት ነበር። በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግስት የጽድቅ አመራር ሰፍኖ ነበር። የሰው ዘር በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ግን ሰይጣን የምድር ገዥነቱን ከአዳም ወስዶበት፤ አዳም ከእግዚአብሔር በታች ብቻ መሆንና የምድርን ፍጥረታት የመግዛት ሹመቱን አጣ።

እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ሰማይ ሰማያትን ሁሉና ምድርን በሙሉ በፍጹም የበላይነቱ የሚገዛ ቢሆንም በምድር ከሚኖረው የሰው ዘር ጋር ግንኙነቱ ተበላሽቶ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ወደ ዓለም በመምጣት የሰው ዘር ምትክ ሆኖ እስከ መስቀል ሞትና ትንሳኤ ድረስ በሰራው ሥራ ዲያብሎስን ሙሉ በሙሉ፣ ለዘላለምና በማይቀለበስ ሁኔታ አሸንፏል/ድል አድርጓል።

ጌታ ኢየሱስ፣ የሰው ዘር ሁሉ እንደ ቀድሞው፣ በአዳም ሕይወት መጀመሪያ አካባቢ እንደነበረው ከእግዚአብሔር ስልጣን በታች ብቻ እንዲሆን ለማድረግ መጣ። በኃጢአት ምክንያት የተለየን የእግዚአብሔር ክብርና አብሮነት ሊመልስልን መጣ። አማኑኤል ከኛ ጋር ሆነ። ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር መንግስት አመራር መዋቅር የሆነችውን ቤተ-ክርስቲያን ሊመሰርትና የቤተ-ክርስቲያን ራስ (ጌታ/ገዢ) ሊሆን መጣ።

ኢየሱስም ተልእኮውን ፈጽሞ ወደ አብ ሲመለስ በምድር የጀመረውን የእግዚአብሔር መንግስት ስርዓት የሚያስቀጥል አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ላከልን። አሁን መንፈስ ቅዱስ የሰው (የእግዚአብሔር ልጆች) በክርስቶስ ኢየሱስ ምድርን የመግዛት ስልጣን እያስቀጠለ ነው።

ሉቃ 10፡19-20፣ *"እንግዲህ እባቡንና ጊንጡን እንድትረግጡ፣ በጠላትም ኀይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤ የሚጐዳችሁም አንዳች ነገር አይኖርም። [20] ይሁን እንጂ መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚያ ደስ አይበላችሁ፤ ስማችሁ ግን በሰማይ ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።"*

ጌታ ኢየሱስ የዲያቢሎስ ስራ ምን እንደሆነ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል። ዮሐ 10፡10፣ "ሌባው ሊሰርቅ፣ ሊገድልና ሊያጠፋ ብቻ ይመጣል፤ እኔ ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲትረፈረፍላቸው መጥቻለሁ።"

ሌባው የሚሰርቀው ምድርን የመግዛት ሥልጣንን ጨምሮ እግዚአብሔር እጃችን እንዲገቡ ያደረጋቸውና እጃችን ሊያስገባቸው የነበሩ ሕጋዊ በረከቶችን ነው፣ ጌታ ኢየሱስ በዲያብሎስና አጋንንቱ የተቀማን ነጻነት፣ ሰላም፤ ደስታና ዕረፍት እንዲሁም ከነጻነት ጋር ተያያዥ የሆኑ በረከቶች ሁሉ ሊመልስልን መጥቷል።

*ሐሥ 26፥18፣ "አንተም ዐይናቸውን ትከፍታለህ፤ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ትመልሳቸዋለህ፤ እነርሱም የኀጢአትን ይቅርታ ይቀበላሉ፤ በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስት ያገኛሉ።"*

*ማቴ 28፥18፣ "ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ቀርቦ እንዲህ አላቸው፤ "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤"*

ጌታ ኢየሱስ በምድር ሁሉ ላይ የበላይ ባለስልጣን የሆነና ዲያብሎስንና ጊንጡን ሁሉ ያሸነፈ ቢሆንም በጌታ ኢየሱስ ያላመኑትና ያመኑትም ቢሆን ደጋግመው በኃጢአት የሚመላለሱትን በሰይጣን ተጽዕኖ ስር ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህም አልፎ የጌታ የሆኑት ህዝብ ላይ ከእምነታቸው ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ ለማድረግ በተለያየ መንገድ በመዋጋት የሚሰራ መሆኑን የሚታወቅ ነው።

**ረ. በኃጢአታችን ምክንያት ይጠብቀን የነበረውን የእግዚአብሔር ቁጣና የዘላለም ሞት ፍርድ ሊያስወግድልን**

2 ጢሞቴዎስ 1፥10 "አሁን ግን ሞትን ደምስሶ በወንጌል አማካይነት ሕይወትንና ኢመዋቲነትን ወደ ብርሃን ባወጣው በመድኀኒታችን በክርስቶስ ኢየሱስ መምጣት ተገልጦአል።"

*1ኛ ቆሮንቶስ 15፡25-26፣ ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ ሥር እስከሚያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና። [26] የሚደመሰሰውም የመጨረሻው ጠላት ሞት ነው።*

*1ኛ ቆሮ 15፡54፣ "የሚጠፋው የማይጠፋውን፣ የሚሞተውም የማይሞተውን በሚለብስበት ጊዜ፣ "ሞት በድል ተዋጠ" ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል።"*

**3. ሕግን በመፈጸም ጽድቁ የኛ ሆኖ እንዲቆጠር ለማድረግ መጣ፡ -**

ከዚህም በላይ ጌታ ኢየሱስ የስራ ሕግን ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ቃልና ፈቃድ ሁሉ በመታዘዝ ተግባራዊ ስላደረገ ሕግን ለመሻር ሳይሆን ለመፈጸም መጣሁ ብሎ የተናገረውን ሙሉ በሙሉ አከናውኖ ስለ ጨረሰ መስቀል ላይ ተፈጸመ ብሎ ነፍሱን ሰጠ። ይሄን ያደረገው የእርሱ ጽድቅ የኛ ሆኖ እንዲቆጠር ነው።

*ማቴ 5፡17-18 ሕግና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ለመፈጸም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።*

*ዮሐ 19፥30፣ "ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፣ "ተፈጸመ" አለ፤ ራሱን አዘንብሎ፣ መንፈሱን አሳልፎ ሰጠ።"*

*ሮሜ10፥4፣ ለሚያምን ሁሉ ጽድቅ ይሆን ዘንድ ክርስቶስ የህግ ፍጻሜ ነውና።*

**4. ከጠላቶቻችን አድኖ የቀረውን አናንተ ተወጡት ሊለን ሳይሆን በራሳችን በምንም ዓይነት ጥረትና ዋጋ ልናገኘው የማንችለው የዘላለም ሕይወትን ሊሰጠን መጣ፣**

*ዮሐንስ 3፥36 "በወልድ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው፤ በወልድ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በላዩ ይሆናል እንጂ ሕይወትን አያይም።"*

*ሮሜ 6፥23፣ "የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው።"*

***ዮሐንስ 5:20-21**፣ አብ ወልድን ስለሚወድ የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል፤ ትደነቁም ዘንድ ከእነዚህም የሚበልጥ ነገር ያሳየዋል። [21] ምክንያቱም አብ ሙታንን እንደሚያስነሣ፣ ሕይወትንም እንደሚሰጥ፣ ወልድም ደግሞ ለሚፈቅደው ሁሉ ሕይወትን ይሰጣል።*

**የዘላለም ሕይወት የሚሰጥ ምግብና መጠጥ የሆነውን የራሱን ስጋና ደም ሊመግበንና ሊያጠጣን መጣ።**

*ዮሐ 6:53-55፣ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላችሁና ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። [54] ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ፤ [55] ሥጋዬ እውነተኛ ምግብ፣ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና፤* (ይሄ ክፍል በሌላ "**የሕይወት እንጀራ**" በሚል ርዕሰ-ትምህርት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል)።

**5. እግዚአብሔር አብን ሊያሳየን (ሊያስተዋውቀን)።** ዮሐ 14:7-9፣ 12:44-46

**ሀ. ከእግዚአብሔር አብ ጋር በነበረ ጊዜ ያየውን የሰማውን ገለጠ**፦ ዮሐ 1:18፣ ስለ እግዚአብሔር ማንነት የሚያሳውቁ ማስረጃዎች ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በፍጥረተ-ዓለሙ ሁሉ በብሉይ ኪዳን ዘመን በቃሉ ማንነቱን አብራርቶ የገለጠባቸው ሁኔታዎች ነበሩ (ምሳሌ፦ ኢሳ 43፡1-13)። ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር እንደ አሁኑ በተሟላ ሁኔታ የሚገልጡ አልነበሩም። ከኢየሱስስ በቀር አብን ያየ ማንም ስለሌለ እርሱ ከአብ ጋር በነበረ ጊዜ ስለ አብ ማንነት ፊት ለፊት ያየውን ከእርሱም የሰማውን ስለተናገረ የተናገረው ሁሉ የአብ ማንነት በግልጽ የሚያሳይ/ የሚያሳውቅ ነው።

**ለ. በቃሉ አብን ገለጠ፦** ዮሐ 12:49፣ 7:16፣ ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ ያስተምረው የነበረው ሁሉ ከአብ የሰማውን/አብ ነገረውን እንደሆነ ደጋግሞ ተናግሯል። ንግግር በተናጋሪው ልብ ያለውን፣ ባህርይ፣ ፍላጎት፣ ዕቅድ፣ ማንነት …ወዘተ የሚገልጥ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ የሰጠው ትምህርት የአብን ማንነት ገላጭ ነው የሚሆነው።

**ሐ. በተግባሩ የአብን ኃይል ገለጠ፦** ዮሐ 14:6-11 ኢየሱስ በምድር ያደርጋቸው የነበሩ ድንቅ ሥራዎች የታመሙትን፣ አንካሶችን፣ የታወሩትን፣ መናገርና መስማት የተሳናቸውን በመፈወስ፣ ሙታንን በማስነሳት የሰራቸው ታምራዊ ስራዎች ሁሉ ያደርግ የነበረው አብ ሲሰራ ያሳየውን ነበር። ደግሞም ኢየሱስ በባህርይ ከአብ ጋር አንድ ስለሆነ "እኔን ያየ አብ አየ"; ስላ እርሱን በማየት የአብም ባህርይ ምን እንደሚመስልና ፍቅሩ፣ ምህረቱ፣ ርህራሄው፣ ጸጋው፣ ታምራት አድራጊነቱ… በጎነቱ ሁሉ ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ የሚያሳውቀን ነው። ዮሐ 6:38 የራሱን ፈቃድ ለማድረግ ሳይሆን የአብን ፈቃድ ለማድረግ ስለ መጣ እግዚአብሔርን በመምሰል ሰለ ኖረ የእግዚአብሔርን ማንነት የሚያሳይ መስታወት በመሆኑ።

**መ. የአብን ወደር የሌለው ታላቅ ፍቅር መጠን ሊያሳይ መጣ፦** *ሮሜ 5:7-8፣ 8:32 "ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን ለሁላችን አሳልፎ የሰጠው፤"… 1ዮሐ 4:9-10፣ መኃ መኃ 8:6-7፣ መዝ 36:7 "አምላክ ሆይ ጽኑ/የማይለዋወጠው ፍቅርህ ምንኛ ክቡር ነው፣" ኤር 31:3 "በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ፤" ኢሳ 54:10፣ "ተራሮች ቢናወጡ ኮረብቶችም ከስፍራቸው ቢወገዱ እንኳ ላንቺ ያለኝ ጽኑ ፍቅር አይናወጥም።" (ዮሐ 3:16፣ 17:23፤)*

እግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁ ኢየሱስን ለኛ የመስዋዕት በግ እንዲሆን ወደ ዓለም መላኩ/መስጠቱ ለሰው ልጆች ያለው ፍቅር ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ገላጭ ከሆኑ ነገሮች ዋነኛው ነው። ምድርና የምድር በረከት ሁሉ ለአንድ ሰው ከመስጠት ይበልጣል። ምድርን ጨምሮ በሰማይ ያሉ ከዋክብትና ፕላኔቶች ሁሉ ከመስጠት ይበልጣል። በርከት ያሉ ቅዱሳን መላእክት ለሰው በመገለጥ የምስራች

(እንኳን ደስ ያላችሁ) ያሉበት ጊዜ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ጌታ ኢየሱስ ወደ ዓለም ልኮ በተወለደበትና በትንሳኤው ወቅት ብቻ ነው።

**1ኛ ዮሐንስ 4፡9-10**፣ "እግዚአብሔር ፍቅሩን በመካከላችን የገለጠው እንዲህ ነው፤ እኛ በእርሱ አማካይነት በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ላከ። [10] ፍቅር ይህ ነው፤ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው ሳይሆን እርሱ እንደ ወደደንና ስለ ኀጢአታችን ማስተስረያ ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ ነው።"

1ዮሐ 3፡1፣ "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ አብ አትረፍርፎ ያፈሰሰልን ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው።" ልጆች ስለሆንን የእግዚአብሔር ወራሾች መደረጋችን የሚደንቅ ፍቅሩ አጉልቶ የሚያሳይ ነው።

ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔር አብን ብቻ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስንም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከተጻፈው በላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት ይበልጥ እንዲተታወቅ አድርጓል።

6. **ጌታ ኢየሱስ ራሱ ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው አዳኙ/መሲሁ መሆኑን በተለያየ መንገድ ሊያስተዋውቅ (ሊመሰክር) መጥቷል።**

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ በመለኮታዊ ሙላቱ ለዘላለም በክብር የኖረ ቢሆንም በኃጢአት ወደ ረከሰችው ዓለም ሰው ሆኖ መጥቷል።

መጥምቁ ዮሐንስ ደቀ-መዛሙርቱን ወደ ጌታ አኢየሱስ እንዲህ የሚል ጥያቄ ሰጥቶ ልኳቸው ነበር። **"ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው አንተ ነህ"? ወይስ ሌላ እንጠብቅ"**። ማቴ 1፡1-6-12
ከአዳም ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር በሰጠው የተስፋ ቃል መሰረት መጥምቁ ዮሐንስ ይህን ጥያቄ ወደ ጌታ ኢየሱስ አስከ ላከበት ጊዜ ድረስ በእስራኤል ምድር ይመጣል ተብሎ የሚጠበቅ፣ የሰው ዘር በኃጢአት ምክንያት ከደረሰበት መንፈሳዊ ውድቀትና መዘዙ ሁሉ የሚያስመልጥ አዳኝ ነበር።

መጥምቁ ዮሐንስ እግዚአብሔር የሰጠውን አገልግሎት ይፈጽም በነበረበት ዘመን የመሲሁ መምጣት ይጠባበቅ የነበረው እርሱ ብቻ ሳይሆን የእስራኤል ሕዝብም ጭምር እንደ ነበር ቀጥሎ ያሉት ጥቅሶች ያስረዳሉ።

***ሉቃስ 3፡15-16*** *"በዚያን ዘመን ሕዝቡ ሁሉ የመሲሁን መምጣት በጉጉት ይጠባበቅ ነበር። ስለዚህ ዮሐንስን "ይህ ሰው ምናልባት መሲሁ ይሆንን?" እያሉ ያስቡ ነበር። [16] ዮሐንስ ግን ለሁሉም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ "እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን ከእኔ የሚበረታ ይመጣል፤ እኔም የእርሱን የጫማ ማሰሪያ መፍታት የሚገባኝ አይደለሁም፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል፤" በማለት መስክሯል።*

በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ዘመን ብቻ ሳይሆን ከዚያ በፊትም ለብዙ ዘመናት በተመሳሳይ ሁኔታ የመሲሁ መምጣት እስራኤላዊያን ይጠባበቁ እንደነበር ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ገልጾታል።

***ማቴ 13፥17*** *"እውነት እላችኋለሁ፤ ብዙ ነቢያትና ብዙ ጻድቃን እናንተ የምታዩትን (ጌታ ኢሱስን) ለማየትና የምትሰሙትንም (ቃሉን) ለመስማት ተመኝተው ነበር፤ ግን አልሆነላቸውም።"*
(እግዚአብሔር የወሰነው ጊዜ እስከሚደርስ መጠበቅ የግድ ነበርና)

በእነዚያ የመጠባበቅ ዘመናት ሁሉ ታላላቅ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ማለትም እንደ ሙሴና ኢያሱ ያሉ ካህናት፣ ነብያት፣ ታዋቂ ቅዱሳን ሰዎችም እንዲሁም ቅዱሳን መላዕክትም ነበሩ። ግን እነዚህ ሁሉ ፈጣሪ ሳይሆኑ ፍጥረታት ስለነበሩ ማናቸውም የሰው ዘር ነፍስ መዳን ጉዳይ መፍትሔ የመስጠት ብቃት ስላልነበራቸው አንዳች ነገር ሊያደርጉ አልቻሉም። ስለዚህ ነው መሲሁ ይመጣል

ተብሎ ለረጅም ዘመናት መጠበቅ ግድ የነበረው፡፡ የመለኮት ኃይል ያለው ከእነዚህ ሁሉ እጅግ የበላይ የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ እስኪመጣ መጠበቅ ነበረበት፡፡

ጌታ ኢየሱስ ራሱ ብቻ፣ እርሱ ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው መሲሁ መሆኑን በወንጌላት ውስጥ ከ70 ጊዜ በላይ ተናግሯል፡፡ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፡ - ዮሐ 18:33-37 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

***ዮሐ 4:25-26**፣ ሴትዮዋም፣ "ክርስቶስ የተባለ መሲሕ እንደሚመጣ ዐውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ነገር ይነግረናል" አለችው:: [26] ኢየሱስም፣ "የማነጋግርሽ እኮ እኔ እርሱ ነኝ" ሲል ገልጦ ነገራት::*

***ዮሐ 6:32-36**፣ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፤ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤ እውነተኛውን እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ ግን አባቴ ነው፤ [33] የእግዚአብሔር እንጀራ እርሱ ከሰማይ የሚወርድ፣ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና::" [34] እነርሱም፣ "ጌታ፣ እንግዲያውስ ይህን እንጀራ ሁል ጊዜ ስጠን" አሉት:: [35] ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔም የሚያምን ፈጽሞ አይጠማም:: [36] ነገር ግን እንደ ነገርኋችሁ፣ አይታችሁኛም እንኳ አታምኑም::"*

***ዮሐ 8:22-24**፣ አይሁድም፣ "'እኔ ወደ ምሄድበት ልትመጡ አትችሉም' ያለው ራሱን ሊገድል ይሆን?" አሉ:: [23] እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ ከታች ናችሁ፤ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፤ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም:: [24] በኀጢአታችሁ እንደምትሞቱ ነግሬአችኋለሁ፤ እኔ እርሱ ነኝ ስላችሁ እኔ እርሱ (መሲሁ) እንደሆንሁ ካላመናችሁ፣ በኀጢአታችሁ ትሞታላችሁና::"*

***ዮሐ 10:23-25**፣ ኢየሱስም በቤተ መቅደስ ግቢ፣ በሰሎሞን መመላለሻ ያልፍ ነበር፤*
*[24] አይሁድም ከበውት፣ "እስከ መቼ ልባችንን አንጠልጥለህ ታቈየናለህ? አንተ ክርስቶስ (በግሪክኛ ክርስቶስ ማለት መሲሀ ማለት ነው) ከሆንህ በግልጽ ንገረን" አሉት:: [25] ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሳላቸው፤ "እኔ ነግሬአችሁ ነበር፤ እናንተ ግን አታምኑም፤ በአባቴ ስም የማደርጋቸው ታምራትም ስለ እኔ (እኔ መሲሁ መሆኔን) ይናገራሉ:: (ዮሐ 18:17)*
ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ጌታ ኢየሱስ እርሱ ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው መሲሁ መሆኑን የመሰከረው በሁለት መንገድ ማለትም በቃሉ በመናገርና ማንም ሊያደርጋቸው የማይቻሉ ታምራዊ፤ ድንቅ ስራዎችን በማድረግ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ ስፍራ ታምራዊ ስራዎቹ ምን ያህል ታላቅ ማስረጃዎች እንደሆኑ ለመግለጽ ሲል እንዲህ አለ፡፡

*ዮሐ 10:37-38፣ "አባቴ የሚያደርገውን ባላደርግ አትመኑኝ፤ [38] የማደርገው ከሆነ ግን እኔን ባታምኑኝ እንኳ፣ (በቃሌ የምነግራችሁ ባታምኑ እንኳ) አብ በእኔ እንዳለ እኔም በአብ እንዳለሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ታምራቱን እመኑ::"*

7. **ጌታ ኢየሱስ ራሱ ለኛ ያለው ፍቅር ሊያሳየን፡-** ዮሐ 15:9፣ "አብ እንደ ወደደኝ ሁሉ እኔም ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ::" (ማቴ 20:28፣ዮሐ 15:13፣ ገላ 2:20፣)
ከሰው ምናልባት ከተገኘ ከፍተኛ አድናቆት የሚሰጠው ፍቅር፤ ሰው ለወዳጁ ሲል የሞተ እንደሆነ ነው፡ ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን፣ ገና ጠላቶቹ ሆን ሳለን ስለ እኛ ሕይወቱን አሳልፎ ሊሰጥ/በኛ ፈንታ ሊሞት መጥቷል፡፡

ኤፌሶን 3:18-19፣"የክርስቶስ ፍቅር ስፋቱ፣ ርዝመቱ፣ ከፍታውና ጥልቀቱ ምን ያህል እንደሆነ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር የመገንዘብ ኀይልን እንድታገኙ ነው:: [19] እስከ እግዚአብሔር ሙላት ሁሉ ልክ ደርሳችሁ እንድትሞሉ፣ ከመታወቅ በላይ የሆነውን የክርስቶስን ፍቅር ታውቁም ዘንድ ነው::"
ሉቃ 23:33-34፣ "ቀራንዮ የተባለ ቦታ በደረሱ ጊዜ ሰቀሉት፤ ወንጀለኞቹንም አንዱን በቀኙ፣ ሌላውን በግራው ሰቀሏቸው:: [34] ኢየሱስም፣ "አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" አለ:: እነርሱም ልብሱን በዕጣ ተከፋፈሉት::"

በየትውልዱ ሁሉ የተፈጸመው፣ በብዛቱና በዓይነቱ እየጨመረ፣ ከክፋት ወደ ክፋት በየጊዜው እያደገ የመጣው የሰው ዘር ኃጢአት ሁሉ የእግዚአብሔር አብና የልጁ የኢሱስን ፍቅር ሊቀንስ/ሊለውጥ አልቻለም። እግዚአብሔር በኃጢአት የተበከለው ዓለምን የወደደው ኃጢአተኞችን ለማዳን አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ነው። ጌታ ኢየሱስ በጠላትነት የተነሱበት የአይሁድ መሪዎች ለረጅም ሰዓታት (15 ሰዓታት ለሚሆን ጊዜ) አሰቃቂ ግርፋትና የመስቀል ስቃይ አድርሰውበት እርሱን በመግደል ላይ እያሉ አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው በማለት እንዲጸልይላቸው ያደረገው ከመታወቅ በላይ የሆነ ፍቅሩ ነው።

ለሰው ልጆች ሲል ጸሐይና ጨረቃን ምድርና በውስጧ ያለውን ሁሉ መልካም ነገር የፈጠረና የሰጠው ጌታ፣ ይሄ ሁሉ ያደረገልን ስላላረካው ራሱ ሰው ሊሆንና የራሱን ሕይወት ለሰው መስዋዕት አድርጎ ሊሰጥ መጣ።

8. **እርሱ አምላክ ሆኖ ሳለ በቃልና በተግባር እንደ ባሪያ ዝቅ ብሎ በማገልገል እና የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ፣ በምድራዊ ሕይወታችን እንዴት መመላለስ እንዳለብን ምሳሌ ሊሆነን።**
የአግዚአብሔር አምላካችንና አባታችን የቅድስና ባህርይ ተካፋዮች እንድንሆን ጌታችንን በመምሰል እየተለወጥን መልካም ፍሬ እያፈራን እንድንሄድ ሊያስተምረን።
ጌታ አየሱስ የእውነትና የሕይወት መንገድ ብርሃን በሰዎች ልብ ለማብራት በጨለማና በሞት ጥላ ውስጥ ለነበረ ህዝብ ብርሀን ሊሆን መጣ። ማቴ 4:13-16
ማቴ11:28-29፣ ዮሐ 13:12-15፣ እግር መተጣጠብ/አንዱ ሌላውን እንደ ባሪያ ሆኖ ማገልገል፣ ማቴ 20:25-28 የበላይ የሆነው እንደ ባሪያ ይሁን፣ ዕብ 12:2-3፣ ፊሊጵ 2:2-8 በዚህ መልኩ እውነተኛ ትህትና ገልጦ ለማሳየት መጣ፣

9. **ወደ አብ መቅደስ መድረሻ መንገድና ወደ ዙፋኑ መግቢያ በር ሊሆነን** መጣ።
በምልጃም ረገድ ጭምር ወደ እግዚአብሔር አብ መቅረብ የሚያስችለው መንገድና በር ጥርት አድርጎ ሊያሳየን መጣ፤ የበግ ለምድ ለብሰው/የብርሃን መላእክት መስለው በተለያየ ኃይማኖት ሽፋን የሰው ልጆችን ወደ ጥፋት የሚመሩት የዲያብሎስ ማሳቻ ስልቶችና የሃሰት ትምህርቶች ገሃድ ሊያደርግ። ዮሐ 10:7-9፤ 14:6 መንገዱ እኔ ነኝ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ በኔ በኩል ካሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፣ ሐሥ 4:12፤ ማቴ 24:4-35፣ ዮሐ 10:9።

10. **በሁሉም ነገር ሕዝቡን ለመምሰል ዕብ** 2:14-17
ወንድሞቹ በስጋና በደም እንሚካፈሉ እርሱ ራሱ ያንኑ በመካፈል እንደኛው ሰው ሆነ። ሰው ሆኖም በሞት ላይ ስልጣን የነበረውን ዲያብሎስን በሞቱ እንዲሽርና በእርሱ የሚያመንኑት ከሞት ባርነት ነጻ እንዲያወጣ ነው። ሰይጣን ሰው የሆነውን አዳም አሸንፎ ለሞት ዳርጎ ነበርና በአዳም ዘር የሞት መልአክ/ገዳይ የሆነውን ሰይጣን ስለተሸነፈ ነው ከሞት ነጻ የወጣነው።
በሁሉም ነገር ወንድሞቹን እንዲመስል ያስፈለገበት 2ኛው ምክንያት በሰውና በእ/ር መካከል ሊቀ ካህናት/መካከለኛ መሆን የሚገባው ሰው ስለሆነ እርሱ ራሱ በተፈተነ ጊዜ መከራን ስለተቀበለ የሚፈተኑተን ሊረዳቸው የሚችል መሀሪና ታማኝ ሊቀ-ካህናት ሆኖ እ/ርን ለመገልገልና ለሕዝቡ የኃጢአት ስርየት ለማስገኘት ነው።

11. **የእግዚአብሔር ልጅነት መብትና መንፈስ ቅዱስን ሊሰጠን**፣ የመለኮት ባህርይ ተካፋዮች ሊያደርገን ዮሐ 14:16-17፣ ገላ 4:6፣ 2ጴጥ 1:4
12. **በእግዚአብሔር አብ ዘንድ የሚራራልን ሊቀ-ካህናታችን ሊሆነን**፤ ሮሜ 8:34፣ ዕብ 2:17-18፣ 4:14-15፣ 1ዮሐ 2:1፣ (ሉቃ 22:32) እርሱ ራሱ አምላክ ስለ ሆነ የሚያስፈልገንን ሁሉ ሊሰጠን ቢችልም፤ ባላጋራችን ዲያብሎስ በእግዚአብሔር አብ ፊት በሚከሰን ጊዜ ለእኛ ወግኖ በመስራት የጠላታችንን ስራ ከንቱ የሚያደርግልን መሆኑን የሚያሳይ ነው። ጌታ ኢያሱስ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ አማላጃችን፣ ጠላታችን በሚከሰን ጊዜ ጠበቃችን… ይሆንናል ማለት ሁል ጊዜ እግዚአብሔር አብ ዘንድ እየቀረበ እባክህ ይሄንና ያን አድርግላቸው እያለ የሚጠይቅ ነው ማለት ሳይሆን ስለ እኛ ያፈሰሰውና ወደ ቅድስተ-ቅዱሳን የዞት የገባው ደሙ ሕያውና ስለ እኛ መናገር የሚችል በመሆኑ ነው። ዕብ 12:24

እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር በዕውቀቱና ጥበቡ ታላቅነት በረቀቀ ዲዛይን በእጁ ሰርቶ ያዘጋጀው መገልገያ ዕቃው ሆኖ ሳለ እንደ መገልገያ ዕቃ ብቻ በመቁጠር ፈንታ ያልተገባን የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ከሰው ጋር ሕብረትና የጠበቀ ቀረቤታ እስከ ማድረግ ድረስ ከራሱ በሆነ በቃላት ሊገለጽ በማይችል ፍቅር እንደ ወደደን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም ፍቅሩ ምድርና በውስጧ ያለውን ሰዎች በአሁኑ ጊዜ እርስ በራሳቸው በጦርነት የሚተላለቁበት በረከት ሁሉ ጸሐይና ጨረቃን ጨምሮ በነጻ ለሰው ዘር ከመስጠቱ እጅግ የላቀና የሚያስደንቅ ነው፡፡
ከዚህም አልፎ አንድያ ልጁን ጌታ ኢየሱስን ስለ እኛ ኃጢአት ያውም በሰዎች እጅ አሰቃቂ የመስቀል ስቃይ ተቀብሎ እኛኑ የማዳን ስራ እንዲፈጽምልን መፍቀዱ ከአእምሮ በላይ የሆነው ፍቅሩና መልካምነቱን፣ አልፎ አልፎ ሳይሆን በየዕለቱ ሊያስደንቀን የተገባ እኛም ፍቅራችንን ፈቃዱን ለማድረግ በመትጋት መግለጽ ግድ የሚለን መሆን ያለበት ነው፡፡
ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት ይመጣል እንዳለው መጣ፡፡ ኢሳ 59፡20፣ ኤር 23፡5-6፣
ሲመጣ ያደርጋቸዋል የተባሉት እርሱ መሲሁ ለመሆኑ ማረጋገጫ ምልክቶችና ነገሮች ሁሉ አደረገ፡፡ ዮሐ 17፡4፣ 19፡30
ወደ መጣሁበት ወደ እግዚአብሔር አብ ዘንድ እሄዳለሁ እንዳለው ሄደ፡፡ ዮሐ 7፡33፣ 8፡21፣ 16፡28፣ 17፡11፤
ተመልሼ ልወስዳችሁ እመጣለሁ እንዳለው በእርግጥ ይመጣል፡፡ ማቴ 16፡27፣ ዮሐ 14፡28፡፡ ስሙ ይክበርልን፣አሜን!!

©ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2018 ዓ.ም.